የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት
The Benishangul-Gumuz regional state Administrative council
ቁጥር 1107/ከ-1/ዓ.ሠ.007
Ref.
ቀን 12/8/2007
Date

ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ጽ/ቤት

**ጉዳዩ፣ <u>የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፣</u>**

በዉጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንና ትዉልደ ኢትዮጵያዉያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች በክልሉ ከተሞች የምዝገባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ ረቂቅ መመሪያ ሚያዚያ 8 ቀን 2007 ዓ/ም በተካሄደዉ የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት /ካቢኔ/ መደበኛ ስብሰባ ላይ በአጀንዳነት ቀርቦ ታይቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ካቢኔዉ በቀረበዉ መመሪያ ላይ በጥልቀት ተወያይቶ መመሪያዉን ተቀብሎ አጽቆታል፡፡

ስለዚህ ይኸዉ ታዉቆ መመሪያዉ ሳይዛነፍ በጥንቃቄ ሥራ ላይ እንዲዉል እያሳሰብኩ፣ለአፈጻፀም ያመቹ ዘንድ የፀደቀዉ መመሪያ አንድ ጥራዝ ከዚህ ደበዳቤ ጋር በማያያዝ የተላከ መሆኑን አስታዉቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

Benishangul-Gumuz Regional State Administrative Council

አህመድ ናስር
ርእሰ መስተዳድር

<u>እንዲያዉቁት፣</u>

- ለክቡር ም/ር/መስተዳድር/ከአንድ ጥራዝ ጋር/

  <u>በጽ/ቤቱ፣</u>

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለከተማ ልማትና ኮንስ/ቢሮ/ከአባሪ ጋር/
- ለህ/ሥ/ማ/ማ/ማ/ቢሮ / // /

  <u>አሶሳ፣</u>

## መመሪያ ቁጥር ------/2007 ዓ.ም

## በውጭ □ገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች በክልሉ ከተሞች የምዝገባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩት ኢትዮጵያዉያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን /ዳያስፖራ/ በትውልድ አገራቸው ሁሉ አቀፍ የልማት እንቅስቃሴ ተሣታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል የዳያስፖራ ፖሊሲ ቀርፆ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ በመሆኑ፤

በፖሊሲው ለአንቀጽ 6.5 (2) እንደተጠቀሰው ዳያስፖራው በግልና በማህበር ተደራጅቶ በክልሎች፣በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የቁጠባ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ የመኖሪያ ቤት ስለሚያገኙበት ሁኔታ በጥናት ላይ የተመሠረተ አሠራር እንደሚዘረጋ በተደነገገው እና በአገር አቀፍ የከተማ ቤት አቅርቦት ስትራቴጂ ማዕቀፍ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በውጭ አገር የሚኖሩ የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤት የኅብረት ስራ ማኅበር መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር የቤት ልማት ኘሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በክልሉ ሲካሄድ የምዝገባ ስርዓቱ ወጥነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዉነት ባለው መልኩ ለማካሄድ እንዲቻል የአፈጻጸም መመሪያ መውጣት እንዳለበት በመታመኑ፤

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 59 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ይህንን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች በክልሉ ከተሞች የምዝገባ ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።



Gumuz Regional State Administrative Council

#0647 P.002/023
22/06 2008 17:10